## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

## ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ቁ. 14184

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ውርጌሳ ታደሰ

መልስ ሰጪ፡- አቶ መለሰ ተካ, አቶ ፍሬሰንበት አዝማች
አቶ በቀለ ዴልኬራ, አቶ አለሙ ደልሊቦ
አቶ ከተማ ኢብሣ, አቶ ወ/ሰማያት ዲማ
አቶ ፍቃዱ ራህመቶ, አቶ አማረ ተሰማ
አቶ ኤፌሶን መጋቢ

*በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት በሙግት ተወካይ ለመሆን ስለ ባለጉዳዩ /ከሳሽ/ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ መቅረብ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር ቁጥሮች 73*

አመልካች ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ዕለት በችሎቱ ባለመገኘታቸው ምክንያት ያቀረቡትን ክስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍትሐብሐር ሥነ/ሥርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሠረት በመዝጋቱ እና ይህንኑ ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በአብላጫ ድምጽ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ

ው ሳ ኔ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጣቸው ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡

1. ክስ ያቀረበ ሰው ክሱ የሚዘጋበት ክርክሩን እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡
2. ከተከሣሹ መልስ ለመቀበል የሚያዝ ቀጠሮ ተከሣሹ እንጂ ሕጉ እንደሚያዘው ጉዳዮ የሚሰማበት ቀጠሮ አይደለም
3. መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሳሽ ባይቀርብ ፍ/ቤቱ የተከሳሹን መልስ ተቀብሎ ጉዳዮን ለተከታዩ ክንውን ማዘጋጀት እንጅ ክሱን መዝጋት የለበትም፡፡



ሐምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም

የመ/ቁ. 14184

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- አቶ ውርጌሳ ታደሰ ጠበቃ ህይሉ አግዘው

መልስ ሰጪ፡- አቶ መለሰ ተካ, አቶ ፍሬሰንበት አዝማች
አቶ በቀለ ዴልኬራ, አቶ አለሙ ደልሊቦ
አቶ ከተማ ኢብሣ, አቶ ወ/ሰማያት ዲማ
አቶ ፍቃዱ ራህመቶ, አቶ አማረ ተሰማ
አቶ ኤፌሶን መጋቢ
ሁሉም አልቀረቡም

**<u>ፍርድ</u>**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የህግ ነጥብ አንድ ጉዳይ በይግባኝ ፍ/ቤት በሚታይበት ወቅት ከተከራካሪዎቹ የአንዱ መቅረት የሚያስከትለው በሕጉ የተደነገገ ውጤት ምንድነው? የሚል ነው፡፡ ለዚሁ የሕግ ነጥብ መነሣት ምክንያት የሆነው ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ዕለት በችሎት ባለመገኘታቸው ምክንያት አመልካቾችን በሚመለከት ቀርቦ የነበረውን ይግባኝ በፍትህብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ.73 መሠረት በመዝጋቱ ነው፡፡ አመልካች መዝገቡ ተመልሶ እንዲከፈት ጥያቄ ቢያቀርብም ለባለጉዳዩ መቅረትም ሆነ ለጠበቃው መቅረት የቀረበው ምክንያት በቂ ስላልሆነ የተዘጋው ይግባኝ አይከፈትም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፣ ጉዳዩ በይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበ ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በድምጽ ብልጫ ፀንቷል፡፡

አመልካች ጠበቃ የሰበር አቤቱታ በመቅረቡና ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ መልስ ሰጪ እንዲቀርቡ ታዞ በጉዳዩ መልስ ቀርቦአል፡፡ የመልስ መልስም እንደዚሁ ቀርቦ ከማጎደሩ ጋር ተያይዞአል፡፡

የሰበር ችሎት በዚሁ የቀረበው የሰበር ማመልከቻ መነሻነት መታየት ያለበት ትልቁ የሕግ ትርጉም አንድ ፍርድ ቤት በይግባኝ ደረጃ ይግባኝ ባይ አልቀረበም በማለት የይግባኝ መዝገቡን ለመዝጋት የሚችለው መቼ ነው? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፍትሐብሔር የሙግት ሂደት የሚመራው በፍትህብሔር ሥነ

ሥርዓት ሕግ ጥያቄ መመለስ የሚኖርበት ሕጉ የሚያስቀምጠው ሥርዓት መሠረት ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ የአንዱ ወይም የሌላው ተከራካሪ ፍርድ ቤት በያዘው ቀን ቀጠሮ አለመገኘት የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብም መሠረታዊ ከሆነ ከመክሰስ መብትና ክስ ከመከላከል መብት ጋር እጅጉን የተያያዘ በመሆኑ መስተናገድ የሚኖረበት ሕጉ የሚያስቀምጠው መስፈርት መሠረት ብቻ መሆን የኖረበታል፡፡

የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በከፊል ውድቅ የደረገው የፍትሀብሔር ሥነ ሥርሀት ሕጉን ቁጥር 73 በመጥቀስ ስለሆነ የትዕዛዙን ትክክል መሆን አለመሆ ለመመርመር በዚህ ቁጥር የሰፈረው ድንጋጌ ስለተከራካሪዎች መቅረብና አለመቅረብ የሚደነግጉትን ተዛማጅ ቁጥሮች መመልከት ያስፈልጋል፣ በቁጥር 73 የሰፈረው ድንጋጌ

> ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንሲማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሣሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበት ቢሆን የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ ከሣሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል፡፡

በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው ክስ ያቀረበ ሰው ክሱ የሚዘጋበት የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ በያዘበት ቀን ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ሳይሆን ክርክሩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ቀጠሮ ያልቀረቡ እንደሆነ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በመሠረቱ ማንም ሰው ክስ ሊያጣ ወይም በከፊል ሊቀርበት የሚገባው ሕግ በግልጽ ለይቶ ባሰፈረው ምክንያት ብቻ ነው፡፡ አንድን ጉዳይ ለማየት የተሰየመ ፍ/ቤት የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለመፈፀም በርካታ ቀጠሮዎች እንደሚሰጥ የታወቀ ነው፡፡ ክስ ያቀረበ ሰው በሁሉም ቀጠሮዎች እንዲገኝ የሚጠበቅበት ቢሆንም በተያዘው ቀጠሮ ባለመገኘቱ ምክንያት ያቀረበው ክስ ሊዘጋበት የሚችለው ግን ሕጉ ለይቶና ዘርዝሮ ባስቀመጣቸው ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ብቻ ነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች በቅጡ ለመንዘብ የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን የከሣሽና/ወይም የተከሣሽ አለመቅረብ (non appearance of parties) አስመልክቶ ያስቀመጠውን ሥርዓት ከአጠቃላይ የሙግት ሂደት ጋር አገናዝቦ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡



ከላይ እንደተጠቀሰው በዚህ መዝገብ የሕግ ትርጉም የሚሻው ትልቁ ጥያቄ አንድ ከሣሽ ወይም ይግባኝ ባይ በቀን ቀጠሮ አልቀረብክም ተብሎ ክሱ /ይግባኙ/ የሚዘጋበት መቼ ነው? የሚለው ነው፡፡ ከሕጉ ቁጥሮች 69፣70፣73 ለመገንዘብ እንደሚቻለው ሕጉ በተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ ምክንያት አንድ መዝገብ እንዲዘጋ ወይም ተከሣሹ በሌለበት የነገሩ መሰማት እንዲቀጥል ትዕዛዝ የሚሰጠው ከሣሽ ወይም ተከሣሹ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ እንዲሰማ በተቀጠረው ቀን ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ነው፡፡ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የሚሉትን በቅደም ተከተል እንመልከት፡፡

69(1) ነገሩን ለማየት ፍርድ ቤቱ በወሰነው ቀን ቀጠሮ ከሣሽ ተከሣሾች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቸው ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡ የተከራካሪ ወገኖች መቅረብ እንደተረጋገጠም ክርክሩ መሰማት ይጀምራል፡፡

70 የተከሣሽ ያለመቅረብ
<u>ክርክሩ እንዲሰማ</u> በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ከሣሽ ቀርቦ ተከሣሹ ያልቀረበ እንደሆነ ለጉዳዩ ውሣኔ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሥርዓት ነው፡፡

73 ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሣሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበትም ቢሆን ፍርድ ቤቱ ተከሣሹ በሙሉ ወይም በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ ተከሣሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል፡፡

አንድን ጉዳይ አይቶ ውሣኔ ለመወሰን በርካታ ቀጠሮዎችን ፍርድ ቤት እንደሚሰጥ የሚታወቅ ሲሆን ከነዚህ በርካታ ቀጠሮዎች መካከል በአንዱ ወይም በሌላኛው ወይም በሁለቱም አለመቅረብ ምክንያት ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የባለጉዳዮቹ መቅረት የተከሰተው ጉዳይ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ ለመስማት ቀጠሮ የተያዘበት ቀን ከሌሎች ቀጠሮዎች በተለየ ሁኔታ እንዲታይ ሕግ አውጪው መፈለጉ ግልጽ ነው፡፡ በተለምዶ ብዙ ፍርድ ቤቶች መልስ ለመቀበል ከሣሽ ወይም ተከሣሽ ወምይ ሁለቱም ያልቀረቡ እንደሆነ ፍርድ ቤቶቹ እነዚህን ድንጋጌዎች

በመጥቀስ ጉዳዩ እንዲዘጋ ወይም ተከሣሹ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የሚሰጡ ቢሆንም የድንጋጌዎቹ ይዘት ይህን አሠራር የሚደግፍ አይደለም፡፡ መልስ ለመቀበል የሚያዝ ቀጠሮ ተከሣሹ የጽሁፍ መልሱን ለማቅረብ እንዲችል የሚያዝ ቀጠሮ እንጂ ሕጉ እንደሚያዘው ጉዳዩ የሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ሳይቀርብ ቢቀር ጉዳዩ ለማሰማት በተቀጠረበት ቀን ሳይቀርብ ቀረ ተብሎ መዝገቡ ሊዘጋበት የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ በመሠረቱ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ የሚያዘው በአንድ ጉዳይ ክስ የተመሠረተበት ሰው በጉዳዩ ላይ የቀረበበትን ክስ ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ ሃሣቡን በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማስረጃም ካለው የማሰረጃውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ እንዲያቀርብ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከከሣሹ የሚጠበቅ ክንዋኔ የለም፡፡ ከሣሹ ሳይቀርብ ቀረ እንኳን ቢባል በፍርድ ቤቱ የሥራ ሂደት ላይ የሚያስከትለው መስተጓጐል ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ባይቀርብ የተከሣሹን መልስ ተቀብሎ ለተከታዩ ክንውን ጉዳዩን ከማዘጋጀት አልፎ መዝገቡን ለመርዝጋት በቂ ምክንያት የለም፣ የመዝገብ መዘጋትን ያህል ትልቅ እርምጃ በአንድ ተከሣሽ ላይ ለመውሰድ ቢያንስ በከሣሹ በኩል መፈፀም የነበረበት ነገር ግን ሳይፈፀም የቀረ በህግ የተደገፈ በቂ ምክንያት መኖር አለበት፡፡ የተከሣሽን የጽሁፍ መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ መዝገቡ እንደሚዘጋ የሚገልጽ ድንጋጌ በሥነ ሥርዓት ህጋችን የትኛውም ክፍል አይገኝም፡፡ የህግ ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ የአንድን ተከሣሽ ክስ መዝጋት ደግሞ አግባብ አይሆንም ተከሣሹ ባለመቅረቡ ምክንያት ክሱ እንዲዘጋ ህጉ የሚያዘው ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ከሣሹ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ኑው፡፡ ከሕጉ አደረጃጀትም መገንዘበ እንደሚቻለው ክሱ የሚሰማው የክስና የመከላከያ ጽሁፎች (ከቁጥር 222-240 የፍትብሔር ሥነሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች መሠረት) ልውውጥ ከተከናወነ በኋላ ነው፡፡ የጽሁፉን ልውውጥ የሚመለከተው የሕጉ ክፍል "ስለክስና ስለመከላከያ ጽሁፍ" በሚል ርዕስ ራሱን የቻለ አንድ ክፍል ሲሆን በዚህ የጽሁፍ ልውውጥ በኋላ የሚከተለው ክንውን ደግሞ "ክስን ስለመስማት" በሚል ርዕስ ራሱን በቻለ ሌላ ምዕራፍ የምናገኘው ነው፡፡ (241-273) ከዚህ የህጉ አደረጃጀት የጽሁፍ መልስ የሚቀርብበት ቀነ ቀጠሮ በመርህ ደረጃ የክሱ



መሰማት ከሚከናወንበት ቀነ ቀጠሮ የተለየ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ከህጉ አደረጃጀት ባሻገር የክስ መሰማትን የሚመለከተው የሙግት ሂደት በሁለት የተከፈለ ሲሆን ሁለቱም የከሣሽና የተከሣሽን መገኘት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ የከሣሽና የተከሣሽን መገኘት የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያ ክስ ሊከፈት የሚፈፀመውን ሥነ ሥርዓት (First hearing) ለአብነት መመልከት ይቻላል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 24(1) መሠረት ክሱ መሰማት በሚጀምርበት ቀን ፍርድ ቤቱ የባለጉዳዮቹን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ ክሱንና መልሱን እንደሚያነብና ተከሣሹ መልሱ ላይ የካደውን ነገር ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ በቃል እንደሚጠይቀው ይገልጻል፡፡ የዚሁ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ወይም ስለሱ ሆኖ የቀረበውን ሰው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ጉዳዮች ወይም ሌሎች ነገሮች አብራርቶ ለማስረዳት ጠቃሚና ተገቢ መስሎ በገመተው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ፍርድ ቤቱ ሊመረምራቸው እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከሣሽ ወይም ተከሣሹ እንዲብራራለት የሚፈልገው ጉዳይ ካለ በፍርድ ቤቱ በኩል እንዲጠየቅለት ማድረግ እንደሚችልም በዚሁ ድንጋጌ ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

ይህ የሚያስገነዝበው የመሰማት ሂደት የከሣሽና የተከሣሽ መገኘት የግድ የሚል ተሟጋቾቹም ጭምር የሚሣተፉበት ሂደት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሂደት ፍርድ ቤቱ ባለጉዳዩችንም ጭምር በማነጋገር ጉዳዩን ለዋናው የሙግት ደረጃ የሚያዘጋጅበት በመሆኑ በከሣሹና የተከሣሹ (ወይም የወኪሎቻቸው) መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከሁለቱ የአንዱ አለመገኘት ለሂደቱ መስተጓጐል የሚኖረው ተጽእኖም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ከሌሎች ቀጠሮዎች ይበልጥ ባለጉዳዩች ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ባይቀርቡ የሚከተለው ውጤት ከሌላው የበለጠ ጠንካራ መሆኑ አስፈለጊ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ምዕራፍ 2 (ከቁጥር 241 - 273) ያሉት ሁሉም ድንጋጌዎች የተሟጋቾች አለመገኘት የሚያስከትለውን ውጤት ከመሰማት ሂደት ጋር አያይዘው የሚያቀርቡትም በከፊል በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ለማንኛውም የመሰማት ቀነ ቀጠሮ የተከሣሽን የጽሁፍ መልስ ለመቀበል የሚሰጠው ቀነ ቀጠሮ የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም ክርክሩ የሚሰማበት ወቅት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የተደነገጉትን ደንቦች የተለየ ባህርይና ዓላማ ባለው መልስ የመቀበል ቀነ ቀጠሮ ተፈጻሚ ማድረግ አግባብነት የለውም፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ

ቁጥሮች 69፣70 እና 73 ሥር ያሉት ድንጋጌዎች ለመልስ በተቀጠረበት ቀን ተፈጻሚ ካልሆኑ ከሣሹ ወይም ተከሣሹ ወይም ሁለቱም ሳይቀርቡ የቀረ እንደሆነ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች የትኞቹ ናቸው የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 67፣70፣73 እና ሌሎች ተዛማጅ ድንጋጌዎች ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁለቱም ጉዳዩ ለመሰማት (hearing) በተቀጠረበት ቀን ያልቀረቡ እንደሆነ ብቻ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ (እንደነገሩ ሁኔታ ይግባኝ ባይ) ወይም ተከሣሹ (የይግባኝ መልስ ሰጪ) ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ለሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የሚሆን ሌላ የህግ ድጋፍ መኖር ይኖርበታል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ከ192 እስከ 199 ባሉት ቁጥሮች ፍርድ ቤት እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው ጉዳዮች ሳይፈፀሙ ሲቀሩ ስለሚሰጡ ትዕዛዞች የተለያዩ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በቁጥር 199 ሥር ያለው ድንጋጌ አሁን ለያዝነው ጉዳይ በተለይ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ቁጥር 199(1) ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ መፈፀም ይገባው የነበረው ጉዳይ ያልተፈፀመ ቢሆንም እንኳ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በዚያው ቀን ቀጠሮ የመሰለውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር (2) ደግሞ ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ወገኖች ጉድለት ያልሆነ እንደሆነ ግን ፈርድ ቤቱ ሌላ ቀጠሮ ይሰጣል ይላል፡፡

አንድ ጉዳይ የተከሣሽን መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ያልቀረቡ እንደሆነ (እንደነገሩ ሁነታ ይግባኝ ባይ ወይም መልስ ሰጪ) ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ መስጠት የሚገባቸው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡ ከድንጋጌው ንኡስ አንቀጽ አንድ ለማየት እንደሚቻለው ለቀጠሮ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም በቀረ ቁጥር መዝገብ የሚዘጋበት ሁኔታ እንደሌለ ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ትዕዛዝ የሚሰጠው አንድ ጉዳይ እንዲፈጽም የታዘዘው ወገን ያን የታዘዘውን ጉዳይ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መልሱን እንዲያቀርብ የታዘዘ ተከሣሽ ይህን ክንውን ሳይፈጽም ቢቀር ፍርድ ቤቱ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመለሰውን ይወስናል፡፡ ከሣሹ ከመልስ በተቀጠረበት ቀን ባይቀርብ ግን ከሣሹ እንዲፈጽመው የታነዘዘው



ነገር ስለሌለ ቀጣዩን ክንውን አስመልክቶ ትዕዛዝ ከመስጠት ውጪ የከሣሹን መዝገብ መዝጋት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የተከሣሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ቀን ከሣሹ ያልቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የተከሣሹን የጽሁፍ መልስ ከማህደሩ ጋር አያይዞ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን ቀጠሮ ወስኖ ለዚሁ አስፈላጊ ትዕዛዞችን መስጠት አለበት እንጂ መዝገቡን መዝጋት የለበትም፡፡ ከላይ ተደጋግሞ እንደተገለፀው መዝገብ የሚዘጋው ከሣሹ ጉዳዩን ለመስማት በፍርድ ቤት ቀጠሮ በተያዘበት ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡

የተከራካሪዎች መቅረብን አስመልክቶ በሰፊው ማየት የስፈለግን በያዝነው ጉዳይ ከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ባይን መዝገብ የዘጋው መልስ ለመቀበል በተቀጠረበት ቀን ይግባኝ ባዩ አልቀረበም በማለት የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.73ን በመጥቀሱ ነው፡፡ ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የአሁኑ አመልካች ፍርድ ቤት ሳይቀርብ የቀረውን ጉዳዩን ለማሰማት በተያዘ ቀጠሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ለመዝጋት ምክንያት አድርጐ የጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የሰጠውን ትዕዛዝ ፈጽሞ የሚደግፍ አይደለም፡፡ መልስ ለመቀበል በተያዘው ቀጠሮ ከይግባኝ ባይ የሚጠበቅ ክንውን ስላልነበረም ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን መልስ ተቀብሎ ቀጣዩን ቀጠሮ (ክንውን) በማስመልከት ትዕዛዝ ከሚሰጥ በስተቀር በተከሣሹ ላይ የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 199ን መሠረት በማድረግ የሚሰጠው ትዕዛዝ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካችን ይግባኝ የዘጋው እንዲፈጽም ትዕዛዝ ተሰጥቶት ሳይፈጽመው የቀረ ክንውን ሳይኖርና መዝገብ እንዲዘጋ ሕግ ያስቀመጠውን ሥርዓት ሳይከተል በመሆኑ ይህ ፍርድ ቤት አልተቀበለውም፡፡ መዝገቡን መልሶ ላለመክፈት የሰጠው ምክንያት ስህተት ባይሆንም ፍርድ ቤት የሠራውንና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስተካከል ሲገባው ያለፈውን ግድፈት በሥ.ሥ.ሕ.ቁ 207 እና 211(2) መሠረት ማቀናት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቷል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

(1) ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ.04000 ጥር 21 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.11523 ጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

(2) ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ እንዲከፈት አድርጐ ካቆመበት እንዲቀጥል ታዟል፡፡

(3) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡